# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
## የአቋም መግለጫ

በግንቦቱ 1997 ዓ.ም. ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢሕአዴግ አስከፊ አገዛዝ እንዲወገድለት ፍላገቱና እምነቱ መሆኑን ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ በሰጠው ድምፅ አረጋግጧል:: ይህን እውነታ የተቃዋሚ ድርጅቶች የተገነዘቡት ብቻ ሳይሆን የዓለም አቀፍ ታዛቢዎችም ያረጋገጡት ነው:: ኢሕአዴግ ይህን የሕዝብ ድምፅ በመገልበጥና እኔ አሸነፍኩ በማለት በተነጠቀ የሕዝብ ድምፅ መንግሥት አቋቁሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሌላ የአምስት ዓመት የግፍ አገዛዝ ለመቀጠል ምክር ቤቱን (ፓርላማውን) ለመክፈት እየተጣደፈ ሲሆን በአንጻሩ ሕዝቡ የተነጠቀውን ድምፅ ለማስከበር የሞት የሽረት ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል:: ወቅቱ በአንድ በኩል ኢሕአዴግ በሆነው መንገድ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚሯሯጥበት በሌላ በኩል ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭነቱን ያረጋገጠበትን ድምፁን ላለማስነጠቅና ለማስከበር የሚሟሟትበት የትንቅንቅ ጊዜ ነው::

በዚህ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በተከታታይ የስልክ ጉባዔዎች ሰፊ ውይይቶችን አድርጓል:: በዚሁም መሠረት መስከረም 26 ቀን 1998 ዓ.ም. (October 6, 2005) የስልክ ጉባዔው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን አሳልፏል::

1. በዚህ የአገራችን አሳሳቢ የፖለቲካ ወቅት ኢሕአዴግ በቀየሰውና በተሰረቀና ባልተከበረ የሕዝብ ድምፅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) ውስጥ ገብቶ መቀመጫ መያዝ የሕዝቡን ድምፅና ፍላጎት መርገጥና መሻር ስለሚሆን በኅብረት ደረጃ ወደ ፓርላማ እንዳይገባ በአብላጫ ድምፅ ወስኗል::
2. ኅብረቱ የቆመለትን የሕዝብ ድምፅ የማስከበር ጥያቄ በሰላማዊ÷ በሕጋዊና ፖለቲካዊ ትግል ለማስቀጠል ኅብረቱና ቅንጅቱ ሕዝቡ የሶስት ቀን በቤት ውስጥ የመቀመጥ ሕዝባዊ ተቃውሞ እንዲያደረርግ ጥሪ ማስተላለፋቸው ይታወሳል:: ለከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ኅብረቱና ቅንጅቱ በቀና መንፈስ ድርድር ሲጀምሩ ለጊዜው ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፎ የነበረው ሕዝባዊ ጥሪ እንደገና እንዲታደስ የተወሰነ ሲሆን ለተግባራዊነቱ ቀደም ሲል በተጀመረው በጋራ የመሥራትና የመተባበር መንፈስ መሠረት ከቅንጅቱ ጋር በመመካከር ተፈጻሚ እንዲሆን ለዋናው ጽ/ቤት መመሪያ ተሰጥቷል::
3. ከላይ እንደተጠቀሰው በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ውጥረት ለማርገብና ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እንዲቻል በውጭ ኃይሎች አደራዳሪነት ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ኅብረቱና ቅንጅቱ የጀመሩት ድርድር በገዥው ፓርቲ በኩል በቀና መንፈስ ለመቀጠል እንዳልፈለገ ግልጽ ሆኗል:: በመሆኑም በኅብረቱ የታመነባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች የመደራደሪያ ነጥብ ሆነው ወይይት እንዲካሄድባቸው እስካልተቀበላቸው ድረስ በድርድሩ መቀጠሉ ትርጉም የለሽ በመሆኑ የገዥው ፓርቲና መንግሥት ለድርድሩ መቋረጥ ብቸኛ ተጠያቂ መሆናቸው ግንዛቤ ተወስዶ ድርድሩ እንዲቋረጥ ተወስኗል::

መስከረም 27 ቀን 1998


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር (Tel.No) 251-1530945 Ÿ (Fax)

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645